U.S. Department of Housing and Urban Development
Office of Housing Office of Multifamily Housing Programs

# የመረጃ ሰነድ

## በHUD ለሚታገዙ ነዋሪዎች

## ክፍል 202/162 — የፕሮጀክት እገዛ ውል (Project Assistance Contract, PAC) ክፍል 202/811 — የፕሮጀክት ኪራይ እገዛ ውል (Project Rental Assistance Contract, PRAC)

## "የኪራይ ሒሳብዎ የሚወሰንበት መንገድ"

የቤቶች አስተዳደር ቢሮ (Office of Housing)

**እ.ኤ.አ ሰኔ 2007**

*ይህ የመረጃ ሰነድ ባለቤቱ/የአስተዳደር ወኪሉ (Owner/Management Agents, OA) እና በHUD የሚታገዙ ነዋሪዎች ገቢን ይፋ ማድረግንና ማረጋገጥን በተመለከተ ያሉትን ኃላፊነቶች እና መብቶችን እንዲያውቁ አጠቃላይ መመሪያ ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።*

## ገቢንና ኪራይን በትክክል ማረጋገጡ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት

የቤቶችና የከተማ ልማት መምሪያ (Department of Housing and Urban Development, HUD) ያካሄዳቸው ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ብዙ ነዋሪ ቤተሰቦች የሚከፍሉት ኪራይ የተሳሳተ ነው። የዚህ ችግር ዋነኞቹ መንስኤዎች የሚከተሉት ናቸው፦

- ነዋሪ ቤተሰቦች ገቢያቸውን ቀንሰው ሪፖርት ማድረጋቸው እንዲሁም
- OA ለነዋሪ ቤተሰቦች ነጻ የሚደረጉላቸውንና ቅናሽ የሚያገኙባቸውን ነገሮች ሳይሰጡ መቅረታቸው።

OAንና ነዋሪዎች በሙሉ ትክክለኛው የኪራይ መጠን መከፈሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

### የOA ኃላፊነት፦

- ትክክለኛ የገቢ መረጃ ማሰባሰብ
- የነዋሪውን ገቢ ማረጋገጥ
- ነዋሪዎች ሊደግላቸው የሚገባውን ቅናሽ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ
- የተከራዩን የኪራይ ሒሳብ በትክክል ማስላት
- ለተከራዩ የኪራይ ውሉን እንዲሁም የገቢና የኪራይ አወሳሰኑን ቅጂ መስጠት
- በቤተሰብ አወቃቀር ረገድ ለውጥ ሲኖር እንዲሁም ገቢው በወር በ200 ዶላርና ከዚያም በላይ መቀነስ ወይም መጨመር ሲያሳይ ኪራዩን በድጋሚ ማስላት
- ስለ OA ፖሊሲዎች ጥያቄ ሲቀርብ መረጃ መስጠት
- ገቢን ማሳወቅን ወይም የኪራይ አወሳሰንን በተመለከቱ መመዘኛዎች ወይም አሠራሮች ረገድ ለውጥ ሲኖር ለነዋሪዎች ማሳወቅ

### የነዋሪዎች ኃላፊነት፦

- ትክክለኛውን የቤተሰብ አወቃቀር መረጃ መስጠት
- ሁሉንም ገቢ ሪፖርት ማድረግ
- ገቢና ወጪዎችን የሚያሳዩ የወረቀት፣ የቅጾችና የደረሰኞች ቅጂዎችን ማስቀመጥ
- በየዓመቱ ከሚካሄዱት የድጋሚ ማረጋገጫ የሥራ ሂደቶች መካከል የሚከሰቱ የቤተሰብ አወቃቀርና የገቢ ለውጦችን ሪፖርት ማድረግ
- ገቢን ለማረጋገጥ የስምምነት ቅጾችን መፈረም
- የኪራይ ግዴታዎችን እና የቤት ደንቦችን መከተል

## የገቢ አወሳሰን

ቤተሰቡ ያገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ጠቅላላ ገቢ ብቁ መሆን አለመሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቡ የሚከፍለውን የኪራይ መጠንና የሚያገኘውንም ድጎማ ይወስናል። ቤተሰቡ በቀጣዮቹ አሥራ ሁለት (12) ወራት የሚያገኛቸው ተቀናሾች እንደተጠበቁ ሆነው ያገኛል ተብሎ የሚታሰበው ገቢ የቤተሰቡን ኪራይ መጠን ለመወሰን ያገለግላል።

### ዓመታዊ ገቢ የሚባለው ምንድን ነው?

ጠቅላላ ገቢ — የገቢ ተቀናሾች = ዓመታዊ ገቢ

### የተስተካከለ ገቢ የሚባለው ምንድን ነው?

ዓመታዊ ገቢ — ተቀናሾች = የተስተካከለ ገቢ

## የተከራዮችን የኪራይ ክፍያ መወሰን

አንድ ቤተሰብ የሚከፍለው የኪራይ መጠን ከሚከተሉት **ከፍተኛ** ሆኖ የተገኘው ይሆናል፦

- *ከተስተካከለው* የቤተሰቡ ወርኃዊ ገቢ 30%
- ከቤተሰቡ ወርኃዊ ገቢ 10%
- ቤተሰቡ የቤት ኪራይ ወጪውን እንዲሸፍን ለማገዝ ከኤጀንሲ የሚሰጥ የማኅበራዊ ድጎማ ኪራይ ወይም የማኅበራዊ ድጎማ ክፍያ።

ማሳሰቢያ፦ አንድ ባለቤት አንድን አመልካች ለPAC ፕሮግራም ሊቀበለው የሚችለው አጠቃላዩ የተከራይ ክፍያ ከጠቅላላው የኪራይ መጠን ያነሰ እንደሆነ ብቻ ነው። ይህ ማስታወሻ የPRAC ፕሮግራምን አይመለከትም። በአንዳንድ የPRAC ፕሮግራም ሁኔታዎች የተከራዩ አጠቃላይ የተከራይ ክፍያ ከPRAC ኪራይ (ጠቅላላ ኪራይ) ይበልጣል።

## ገቢና ንብረቶች

በHUD የሚታገዙ ነዋሪዎች ከማንኛውም ምንጭ የሚያገኙትን ገቢያቸውን **በሙሉ** ለባለቤቱ ወይም ለወኪሉ (OA) ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። የገቢ ተቀናሾች የተከራዮች ኪራይ ሂደት አካል ነው።

በዓመታዊ ገቢ ውስጥ የሚካተተው ከንብረቶች የተገኘ ገቢ መጠን ሲወሰን የንብረቱ የጥሬ ገንዘብ ዋጋ ከ5000 ዶላር በላይ እስካልሆነ ድረስ ከንብረቱ የተገኘው ገቢ እንዲካተት ይደረጋል፤ ከዚያ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ በዓመታዊ ገቢ ውስጥ እንዲካተት የሚደረገው መጠን ከጠቅላላው ንብረት 2% እና ከንብረቱ ከሚገኘው ጠቅላላ ገቢ በልጦ የተገኘው ይወሰዳል።

ዓመታዊው ገቢ የሚከተሉትን ያካትታል፦

- የምንዳና የደሞዝ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ የኮሚሽን፣ የማበረታቻ ስጦታ (ቲፕ) እና የጉርሻ (ቦነስ) እንዲሁም የሌሎች የግል አገልግሎቶች ክፍያ ሙሉ መጠን (ከደሞዝ ክፍያ ተቀናሽ በፊት)
- ከንግድ ሥራ ወይም ከሙያ የሚገኝ የተጣራ ገቢ
- ወለድ፣ ትርፍ እና ሌሎች ከቋሚ ወይም ከግል ንብረት የሚገኙ ማንኛውም ዓይነት የተጣሩ ገቢዎች (ከዚህ በታች ያለውን ንብረቶች የሚያካትቱት/ንብረቶች የማያካትቱት የሚለውን ይመልከቱ)
- ከማኅበራዊ ዋስትና፣ ከአበል፣ ከኢንሹራንስ ፖሊሲዎች፣ ከጡረታ ሒሳብ፣ ከጡረታ አበል፣ ከአካል ጉዳት ወይም ከሞት ካሳ እንዲሁም ወቅታዊ ክፍያዎች በመዘግየታቸው ምክንያት የሚሰጠውን የአንድ ጊዜ የተጠራቀመ ክፍያ ወይም በየወሩ እንደሚከፈል ቃል የሚገባውን ጨምሮ ተመሳሳይ ወቅታዊ ክፍያዎች **(በየጊዜው የሚከፈሉና የዘገዩ የተጨማሪ ዋስትና ገቢ እና የማኅበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅሞችን አይጨምርም፤ የዓመታዊ ገቢ ተቀናሾች የሚለውን ከዚህ በታች ያለውን ክፍል ይመልከቱ)**
- በገቢ ምትክ የሚሰጡ እንደ ሥራ አጥነትና የአካል ጉዳተኝነት ድጎማ፣ የሠራተኞች ድጎማ እና የሥራ መልቀቂያ ክፍያ ያሉ ክፍያዎች **(የቤተሰብ ንብረት ላይ በአንድ ጊዜ የሚጨመርን መጠን አይጨምርም፤ የዓመታዊ ገቢ ተቀናሾች የሚለውን ከዚህ በታች ያለውን ክፍል ይመልከቱ)**
- ማኅበራዊ ድጎማ
- እንደ የልጆች ድጋፍ ክፍያና እንዲሁም ከድርጅቶች ወይም ቤቱ ውስጥ ከማይኖሩ ግለሰቦች የሚደረግ መደበኛ መዋጮ ወይም እንደ ስጦታ ያለ በየጊዜው የሚሰጥና ተቆራጭ አበል
- ለጦር ሠራዊት አባላት የሚሰጡ ሁሉም መደበኛ፣ ክፍያዎች፣ ልዩ ክፍያዎችና አበሎች (በጠላት የጦር ጥቃት ስለተሰነዘረባቸው የሚሰጠውን ልዩ ክፍያ አይጨምርም)
- **ለክፍል 8 (Section 8) ፕሮግራም ብቻ፣ አንድ ሰው በከፍተኛ ትምህርት ደንብ 1965 (Higher Education Act of 1965) መሠረት የሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ ለትምህርት ከሚያስፈልገው መጠን ያለፈ ሲሆን ግለሰቡ ለራሱ ገቢ እንዳገኘ ይቆጠራል። ይህ የገንዘብ ድጋፍ እንደ ግለሰቦቹ ዓመታዊ ገቢ የማይቆጠረው ግለሰቦቹ ዕድሜቸው ከ23 ዓመት በላይ ሆነው የእነርሱ ጥገኛ የሆኑ ልጆች ያሏቸው እንደሆነ ወይም ተማሪው የሚኖረው የክፍል 8ን እገዛ ከሚያገኙ ወላጆቹ ጋር የሆነ እንደሆነ ነው። ለዚህ አንቀጽ ዓላማ ሲባል "የገንዘብ ድጋፍ" የሚለው መግለጫ በገቢ አወሳሰን ረገድ ብድርን አይጨምርም። **

ንብረቶች የሚያካትቱት፦

- ስቶኮች፣ ቦንዶች፣ የግምጃ ቤት ሰነዶች፣ የማከማቻ ሰርቲፊኬቶች፣ የገንዘብ ገበያ ሒሳቦችን
- የግለሰብ ጡረታ እና የKeogh ሒሳቦች
- የጡረታ ሒሳብ
- በቁጠባና በቼክ ሒሳብ፣ በካዝና፣ በቤት ወዘተ የተቀመጠ ገንዘብ
- ግለሰቡ ሳይሞት የገባው የተሟላ የሕይወት መድን ፖሊሲ የጥሬ ገንዘብ ዋጋ
- የኪራይ ንብረት እና ሌሎች ካፒታል ኢንቨስትመንቶች ተመጣጣኝ ዋጋ
- እንደ ኢንቨስትመንት የተያዘ የግል ንብረት
- ተሰብስቦ አንድ ጊዜ የሚከፈል ወይም የአንድ ጊዜ ብቻ ክፍያ
- ሞርጌጅ ወይም በአመልካቹ የተያዘ ዋስትና
- ከሚዛናዊው የገበያ ዋጋ በታች የተላለፉ ንብረቶች።

ንብረቶች የማያካትቱት፦

- አስፈላጊ የሆኑ የግል መገልገያዎች (ልብስ፣ ቁሳቁስ፣ ተሽከርካሪ፣ የጋብቻ ቀለበት፣ የአካል ጉዳት ላለባቸው ግለሰቦች ታስበው የተዘጋጁ ተሽከርካሪዎች)
- የኢንዲያን ትረስት ላንድ ወለዶች
- የተወሰነ ጊዜ የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲዎች
- ቤተሰቡ የሚኖርበት የጋራ መኖሪያ ተመጣጣኝ ዋጋ
- በሥራ ላይ ያለ የንግድ አካል የሆኑ ንብረቶች
- በአግባቡ የባለቤቱ ንብረት ያልሆኑ ወይም በግለሰብ ደረጃ የተያዙ ሆኖም፦
  - የቤተሰቡ አባል ላልሆነ ሌላ ግለሰብ ጥቅም የሚያስገኙ ንብረቶችና የተሰባሰቡ ገቢዎች እንዲሁም
  - ከንብረቶቹ ለተገኘው ገቢ የገቢ ቀረጡን የመክፈሉ ኃላፊነት የሌላ ግለሰብ ከሆነ
- አመልካቹ ተጠቃሚ ያልሆነባቸው እንዲሁም ለአመልካቹ ምንም ገቢ የማያገኙ ንብረቶች (ለምሳሌ፦ ድብደባ የደረሰባት ሴት ከባለቤቷ ጋር የጋራ ንብረት የሆነ ቤት አላት። በቤት ውስጥ ካለው ሁኔታ የተነሳ ከንብረቱ የምታገኘው ምንም ገቢ የለም እንዲሁም ንብረቱን ወደ

ጥሬ ገንዘብም መቀየር አትችልም።)

- በሚከተሉት ምክንያቶች ከገበያው ሚዛናዊ ዋጋ በታች በሆነ ዋጋ የተላለፉ ንብረቶች፦
  - የባንክ ዕዳ
  - ኪሳራ
  - የፍቺ ወይም መለያየት ስምምት፤ አመልካቹ ወይም ነዋሪው የግድ በዶላርም ባይሆን የማካካሻ ክፍያ ካገኙ።

በዓመታዊ ገቢ የማይካተቱ፦

- ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች (የማደጎ ልጆችን ጨምሮ) ተቀጥረው የሚያገኙት ገቢ
- የማደጎ ልጆችን ወይም አዋቂዎችን (ብዙውን ጊዜ የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች፣ ከተከራዩ ቤተሰብ ጋር ዝምድና የሌላቸው፣ ብቻቸውን መኖር የማይችሉ) ለመንከባከብ ሲባል የተገኘ ገንዘብ
- እንደ ውርስ፣ የኢንሹራንስ ክፍያ ያለ (የጤናና የአደጋ ኢንሹራንስ እንዲሁም የሠራተኖች ካሳን ጨምሮ) ከቤተሰቡ ንብረቶች ተጨማሪ የሆነና የተጠራቀመ የገንዘብ መጠን፣ የካፒታል ትርፍ እንዲሁም የግል ወይም የንብረት ኪሳራ ማካካሻ
- ለማንኛውም የቤተሰቡ አባል ሕክምና ወጪ ወይም የሕክምና ወጪውን ለመተካት ታስቦ ለቤተሰቡ የተሰጠ የገንዘብ መጠን
- ከሊቭ-ኢን (live-in) ድጋፍ የተገኘ ገቢ
- **ከላይ ባለው ዓመታዊ ገቢ ያሚያካትተው በሚለው ሥር እንዳለው ለከፍተኛ የትምህርት ተቋም የተመዘገቡ ተማሪዎች በክፍል 8 (Section 8) ፕሮግራም ገቢ ውስጥ የሚካተቱ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ** በቀጥታ ለተማሪውም ይሁን ለትምህርት ተቋሙ የተከፈለ ለተማሪ የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በሙሉ
- በጦር ሰራዊት ውስጥ ለሚያገለግልና በጠላት የጦር ጥቃት ለደረሰበት የቤተሰብ አባል የሚሰጥ ልዩ ክፍያ
- በHUD የገንዘብ ድጋፍ ከሚንቀሳቀስ የስልጠና ፕሮግራም የሚገኝ የገንዘብ መጠን
- ራስን ለመቻል የሚያበቃ እቅድ (Plan to Attain Self-Sufficiency, PASS) መሠረት ለአገልግሎት ተለይተው በመቆየታቸው ምክንያት ለተጨማሪ የዋስትና ገቢ ብቁ እንዲሆኑና ጥቅማ ጥቅሞችን እንዲያገኙ ሲባል ለተወሰነ ጊዜ የተገለሉ የአካል ጉዳተኛ ሰዎች የሚያገኙት የገንዘብ መጠን
- በሌላ የሕዝብ ፕሮግራም የታሳታፊ ግለሰብ ከኪሱ ያወጣውን ወጪ (ልዩ መገልገያ፣ ልብስ፣ መጓጓዣ፣ የልጆች እንክብካቤ ወዘተ) ለመሸፈን ወይም ለመተካት የሚሰጥና በተወሰነ ፕሮግራም ውስጥ መሳተፍ እንዲቻል ሲባል ብቻ የሚሰጥ ክፍያ
- የነዋሪ አገልግሎት ክፍያ (በወር ከ$200 በላይ መብለጥ የለበትም)
- ማንኛውም የቤተሰብ አባል በብቃት ማሳደጊያ የግዛቱ ወይም የአካባቢው የቅጥር ስልጠና ላይ በመካፈሉ እንዲሁም የቤተሰብ አባል የነዋሪዎች አስተዳደር ሠራተኛ በመሆን በወሰደው ስልጠና ምክንያት የሚገኝ የገቢ ጭማሪ
- ጊዜያዊ፣ የማይደጋገም ወይም መደበኛ ያልሆነ ገቢ (ስጦታን ጨምሮ)
- በናዚ ዘመን ስደት የደረሰባቸው ሰዎች በመንግሥቱ ሕግ መሠረት ባቀረቡት የይገባኛል ጥያቄ መሠረት አንድ የውጭ መንግሥት የሚከፍለው ክፍያ
- እያንዳንዱ 18 ዓመት የሞላው ወይም ከዚይ በላይ የሆነው የሙሉ ቀን ተማሪ ልጅ የሚያገኘው ከ480 ዶላር የበለጠ ገንዘብ (የቤተሰቡን አስተዳዳሪ፣ ረዳት አስተዳዳሪ ወይም የትዳር ጓደኛ አይጨምርም)
- በእያንዳንዱ የጉዲፈቻ ልጅ ከ480 ዶላር በላይ የሆነ የጉዲፈቻ እገዛ ክፍያ
- ሰብሰብ ብሎ የተከፈለ የተጨማሪ ዋስትና ገቢ እና የማኅበራዊ ዋስትና ጥቅማ ጥቅም ወይም በየወሩ እንደሚከፈል ቃል የተገባ መጠን
- በግዛቱ ሕግ መሠረት ለመኖሪያ ቤታቸው የተከፈለ የንብረት ቀረጥ ተመላሽ ክፍያ ሆኖ ለቤተሰቡ የተከፈለ
- በአእምሮአዊ እድገት ረገድ የአካል ጉዳት ያለበት የቤተሰብ አባል ቤት ውስጥ የሚኖርበት ቤተሰብ የአእምሮአዊ እድገት ጉድለት ያለበትን ቤተሰቡን አባል ቤት ውስጥ ለማስቀመጥ የሚስፈልጉትን አገልግሎቶችና መገልገያዎች ወጪ ለማቅለል ሲባል የሚሰጥ ክፍያ ተጠቃሚ የሆነ ቤተሰብ

በፌዴራል ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ ተቀናሾች፦

- በምግብ ኩፖን ደንብ 1977 (Food Stamp Act of 1977) መሠረት ብቁ ሆኖለተገኘ ቤተሰብ የሚሰጥ የተወሰነ ዋጋ
- በቤት ውስጥ በጎ ፈቃደኛ ሠራተኞች አገልግሎት ደንብ 1973 (Domestic Volunteer Services Act of 1973) መሠረት ለበጎ ፈቃደኛ ሠራተኞች የሚሠጥ ክፍያ
- በመጀመሪያ የአላስካ ሰፋሪዎች ካሳ ህግ (Alaska Native Claims Settlement Act) መሠረት የተገኘ ክፍያ
- ለአንዳንድ የሕንድ ጎሳዎች ከተያዙ የዩኤስ የድንበር አካባቢ ቦታዎች የተገኘ ገቢ
- በጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንት (Department of Health and Human Services) በሚያካሂደው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤቶች የኃይል እገዛ ፕሮግራም (Low-Income Home Energy Assistance Program) መሠረት የተገኘ ክፍያ ወይም አበል
- ሙሉ በሙሉም ይሁን በከፊል በሥራ ስልጠና አጋርነት ደንብ (Job Training Partnership Act) የገንዘብ ድጋፍ በሚደረግላቸው ፕሮግራሞች የተገኘ ክፍያ
- ለኦታዋ ሕንዳውያን ግራንድ ሪቨር ባንድ ከተመደበ የገንዘብ ድጋፍ ላይ የተገኘ ክፍያ
- በሕንዳውያን የይገባኛል ጥያቄ ኮሚሽን (Indian Claims Commission) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ የይገባኛል ጥያቄ ማስተናገጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከተገኘው ሒሳብ በእያንዳንዱ ድርሻ ውስጥ የመጀመሪያው 2000 ዶላር፣ በሕንዳውያን የባላደራነት ይዞታ ወይም የተከለለ ቦታ ላይ የሚገኙ ግለሰብ ሕንዳውያን ወለድ፣ ይህም በእነዚህ የባላደራነት ወይም የተከለሉ ቦታዎች ከተያዘ ወለድ ከሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦች

ከዓመት ገቢያቸው ላይ የሚከፍሉትን 2000 ዶላር ይጨምራል።

- በፌደራሉ የሥራ-ጥናት ፕሮግራም (Federal work-study program) ወይም በሕንዳውያን ጉዳይ ቢሮ የተማሪዎች እገዛ ፕሮግራሞች አማካኝነት የሚሰጡትን ሽልማቶች ጨምሮ በከፍተኛ ትምህርት ደንብ 1965 (Higher Education Act of 1965) ምዕራፍ 4 መሠረት በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጡ ነጻ የትምህርት ዕድሎች ክፍያ መጠን
- በአረጋውያን አሜሪካውያን ደንብ 1985 (Older Americans Act of 1985) ምዕራፍ 5 መሠረት የገንዘብ ድጋፍ ካላቸው ፕሮግራሞች የሚገኙ ክፍያዎች
- እ.ኤ.አ ጥር 1 ቀን 1989 ወይም ከዚያ በኋላ ከAgent Orange Settlement Fund ወይም በ*In Re Agent* የምርት ተጠያቂነት ሕጋዊ ድንጋጌ መሠረት የተገኘ ማንኛውም ክፍያ
- በMaine Indian Claims Settlement Act of 1980 መሠረት የተገኘ ክፍያ
- በልጆች እንክብካቤና እድገት ብሎክ ግራንት ደንብ 1990 (Child Care and Development Block Grant Act of 1990) መሠረት የሚሰጥ ወይም የሚመቻች የማንኛውም የልጆች እንክብካቤ ዋጋ (እንዲህ ካለው እንክብካቤ የሚገኝ ማንኛውም ክፍያ ወይም ለእንዲህ ዓይነቱ እንክብካቤ የወጣውን ወጪ ለመተካት የሚሰጥ ክፍያ)
- የገቢ ቀረጥ ክሬዲት (EITC) ተመላሽ ክፍያ ሆኖ እኤአ ጥር 1 ቀን 1991 ወይም ከዚያ በኋላ የተከፈለ
- የሕንዳውያን የይገባኛል ጥያቄ ኮሚሽን ለኮንፌዴሬሽን ጎሳዎች እና ለያኪማ የሕንድ ብሔር ወይም ለሜስካሌሮ ሪዘርቬሽን የአፓቼ ጎሳ የሚከፍለው ክፍያ
- በብሔራዊና ማኅበረሰባዊ አገልግሎቶች ደንብ 1990 (National and Community Service Act of 1990) መሠረት ለAmeriCorps ተሳታፊዎች የሚከፈል አበል፣ ገቢና ክፍያ
- በ38U.S.C. 1805 ድንጋጌ መሠረት የቬትናም ጦርነት ተመላሽ ልጅ ለሆነና በስፓይና ቢፊዳ ለሚሠቃይ ልጅ የሚከፈል ማንኛውም አበል
- የወንጀል ድርጊት ሰለባዎች ደንብ (Victims of Crime Act) በሚደነግገው መሠረት አመልካቹ የወንጀል ድርጊት ሰለባ በመሆኑ ምክንያት የወንጀል ድርጊት ሰለባ ለሆነ ሰው (በወንጀል ድርጊት ሰለባዎች ደንብ (Victims of Crime Act) መሠረት) በካሳ መልክ በወንጀል ድርጊት ሰለባዎች እገዛ ፕሮግራም አማካኝነት (ወይም ክፍያ ወይም የእንዲህ ዓይነቱን ወጪ ለመሸፈን የሚሰጥ ክፍያ) የሚሰጥ ማንኛውም የገንዘብ መጠን
- በሰው ኃይል ኢንቨስትመንት ደንብ 1998 (Workforce Investment Act of 1998) መሠረት ተሳትፎ ለሚያደርጉ ግለሰቦች የሚሰጥ አበል፣ ገቢ እና ክፍያ።
- የጦርነት ተመላሾች ጉዳይ ዲፓርትመንት የሚሰጠው የተጠራቀመ የአካል ጉዳተኝነት ጥቅማ ጥቅም ወይም የመኖሪያ ቤቶችና የኤኮኖሚ ማገገሚያ ደንብ 2008 (Housing and Economic Recovery Act of 2008, HERA) መሠረት በየወሩ እንደሚያገኝ ቃል የተገባለት ክፍያ መጠን።

## ተቀናሾች፦

- የሙሉ ቀን ተማሪዎችን ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸውን ግለሰቦች ጨምሮ ለእያንዳንዱ ጥገኛ 480 ዶላር
- ለማንኛውም አረጋዊ ቤተሰብ ወይም የአካል ጉዳተኛ ቤተሰብ 400 ዶላር
- ከዓመታዊው ገቢ ከ3% በላይ የሚሆን የማንኛውም የአረጋዊ ወይም የአካል ጉዳተኛ ቤተሰብ ያልተተካ የሕክምና ወጪ
- የቤተሰቡ አባል(ላት) ከዓመታዊው ገቢ 3% በላይ እንዲሠሩ ለማስቻል የወጣና ያልተተካ መጠነኛ የተንከባካቢ እና የአካል ጉዳተኛ ቤተሰብ አባላት የአጋዥ መሳሪያዎች ወጪ
- አንድ የአረጋዊ ቤተሰብ ያልተተካ የሕክምና ወጪና የአካል ጉዳተኞች እገዛ ወጪዎች ካሉት የገቢ ወጪዎች 3% የሚሠላው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።
- የቤተሰቡ አባል መካከል የሚቀጠር ወይም ትምህርቱን የሚቀጥል ሰው እንዲኖር ለስማቻል ዕድሜያቸው ከ13 ዓመት በታች ለመሆኑ ልጆች ማንኛውም መጠነኛ የሆነ የልጆች እንክብካቤ ወጪ።

## ማመሳከሪያ ጽሑፎች

ደንቦች፦

- አጠቃላይ የHUD ፕሮግራም መስፈርት፤ 24CFR ክፍል 5 (General HUD Program Requirements; 24 CFR Part 5 and CFR 24 Part 891)

የመመሪያ ጥራዝ፦

- 4350.3 የገንዘብ ድጎማ የሚደረግባቸው የባለ ብዙ ቤተሰብ መኖሪያዎች ፕሮግራም ይዞታ መስፈርት (4350.3, Occupancy Requirements of Subsidized Multifamily Housing Programs)

ማሳሰቢያዎች፦

- "በፌዴራል ደረጃ የተፈቀዱ ተቀናሾች" Notice 66 FR 4669፡ ሚያዝያ 20/ 2001 ("Federally Mandated Exclusions" Notice 66 FR 4669, April 20, 2001)

ለተጨማሪ መረጃ፦

ስለ HUD ፕሮግራሞች በHUD የኢንተርኔት አድራሻ ዋና ገጽ ላይ፡ http://www.hud.gov በሚለው ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።